# [...በህሉል...]

ወሃብ ኢብኑ አምር ይባላል፡ ኩፋ ውስጥ ተወልዶ ነው ያደገው። በሃሩን አል-ረሺድ የንግስና ዘመን ይኖር የነበረው ይህ ሰው በህሉል በሚል ቅፅል ስም ይታወቃል። ኢማም ሙሳ ካዚም ከሃሩን አል-ረሺድ ጋር ባለመግባባታቸው ሰበብ የቅርብ ተማሪዎቻቸውና ባልደረቦቻቸው ምን ብናደርግ ይበጀናል? ሲሉ ኢማሙን አማከሩ። ኢማም ሙሳ በአንዲት ፊደል ምላሽ ሰጡ። እሷም ፊደል ጂም(ج) ነበረች። ሶስቱም ጓደኞቻቸው ተጨማሪ ማብራርያ አልጠየቁም፡ መልስ አግኝተው ወደየመጡበት ተመለሱ። የመጀመርያው ሰው ጂም'ን "ጀለኡል ወጠን"~ ከአገር መሸሽ ማለት ነው ሲል ተረድቶ ከበግዳድ ወደ ሌላ ከተማ ሄደ። ሁለተኛው የኢማሙ ባልደረባ "ጀበል" ማለት ነው ብሎ ኑሮውን ከተራራ ማዶ መግፋት ጀመረ። ሶስተኛው ሰው፡ ባለ ታሪካችን በህሉል ደግሞ "ጁኑን" ~ እብደት ማለት ነው አለ። ከዛን ቀን በኋላም እንዳ'በደ ሰው መሆን ጀመረ። ወላጆቹ ከበርቴና ባለሀብት ነበሩ፡ ኒዛማባድ እስከ 1301 እ.ኤ.አ ከአባቱና ከተለያዩ ዓሊሞች እውቀት ቀስሟል። ከፋርስ እስከ ዐረብ ግብረ-ገብ እና ተሰውፍን ተምሮ በሀያ አመቱ የመስጂድ ኢማም ሁኖ ተሹሟል። በህሉል እንደ እብድ ከመከወኑ በፊት የድሎት ህይወት ነበረው፡ ቃዲ/ዳኛም ሆኖ አገልግሏል። የኢማሙን ትእዛዝ ሲቀበል ግርማዊነቱን እርግፍ አድርጎ ተወው፡ ከዝች ዓለም ጣጣ ራሱን አውጥቶ በአላህ መንገድ "አበደ"።

አንድ ቀን ቁርጥራጭ ጨርቅ ለብሶ ወደ በግዳድ ሜዳ ወጣ፡ ዱላውን ይዞ 'ቹ! ፈረሴ' እያለ እንጨቱን ይጋልብ ጀመር። በቃ በህሉል "አበደ" ተባለ። ከሃሩን

Edit with WPS Office

ቤተ-መንግስት ይልቅ ሰው የማይኖርበትን ጫካ መረጠ። ነገር ግን እዛው መንኖ አልቀረም፡ ብቅ እያለ ማስተማር የፈለገውን አድርሶ ይመለሳል።

**በህሉል የሃሩን ዙፋን ላይ**

አንድ ቀን በህሉል የሃሩን ቤተ-መንግስት ሲገባ ዙፋኑ ባዶ ሆኖ አገኘው፡ ጠባቂዎች ስላልነበሩ ማንም አላስቆመውም በቀጥታ ወደ ዙፋኑ አመራና ሃሩን መቀመጫ ላይ ተደላደለ። ሑራሶች ሲያዩት ተናደው እየደበደቡ እያዋከቡ አባረሩት። በህሉል እንባውን ያዘንብ ጀመር። ሃሩን ደርሶ ሲመለከት ሰዎቹን "በህሉል ለምንድነው የሚያለቅሰው?" ሲል ጠየቀ "እብዱ" በህሉል የሆነውን ተናገረ። ሃሩንም ተቆጥቶ በህሉልን ያባብል ጀመር።

በህሉል "ያለቀስኩት ለራሴ አይደለም" አለው። "እኔ ያለቀስኩት፡ ላ'ንተ ነው። ለጥቂት ሰከንዶች ዙፋንህ ላይ ብቀመጥ ይህን ሁሉ ድብደባና መከራ አስተናገድኩ፡ አንተ ግን ህይወትህን ሙሉ እዚህ ወንበር ላይ ተቀምጠሃል፡ የሚያጋጥምህን መከራ ሳስበው ፈራሁልህ። ምን ይከተለኛል ብለህ አትፈራም?" አለው። ሃሩን በተራው ተንሰቅስቆ ያለቅስ ጀመር።

**************

በህሉል ለአላህ ያደረ ብቁና ድንቅ ዓሊም ነበር፡ ምጡቅ አዕምሮ እና መልካም ባህሪያት የተቸሩት ጥበበኛ ነበር። ለማንኛውም ጥያቄ መልስ አዘጋጅቶ ያስቀመጠ ይመስል ፈጣን ምላሽ ሲሰጥ ሰዎችን ያስገርማል።

Edit with WPS Office

**በህሉልና ቤት አከራዩ**

አንድ ጊዜ በህሉል ወደ በስራ ለጉዳይ ሄዶ ባለበት ለጥቂት ጊዜያት ቤት መከራየት ፈለገ። ያገኘው ቤት አሮጌ በመሆኑ ግድግዳው ያዘነበለ፡ ጣራውም የተሰነጣጠቀ ነበር። በህሉል ወደ ቤቱ ባለቤት ሄዶ ‹‹ያከራየኸኝ ቤት በጣም አስጊ ነው፤ ጣራውና ግድግዳው ተሰነጣጥቀዋል›› አለው። አከራዩም ‹‹ቤቱ ምንም ችግር የለበትም፡ ሁሉም ፍጥረታት አላህን እንደሚያወድሱትና እንደሚያጥራሩት ታውቃለህ አይደል? ይህም የቤቱ መጎንበስ ተስቢህና ምስጋና ነው›› ብሎ በቀልድ መልክ መለሰለት። በህሉልም የዋዛ አይደለምና ‹‹የተናገርከው በሙሉ እውነት ነው፤ ፍጥረታት ጌታቸውን ከማወደስና ከማጥራት በመቀጠል ሱጁድ ይወርዳሉ፤ እኔም የቤቱን ሱጁድ ፈርቼ ነው ቶሎ የምለቀው›› አለው።

*************

ወቅቱ በግዳድ በዒልምም ሆነ ስልጣኔ ጫፍ የደረሰችበት ወርቃማ ዘመን ነበር። የተለያዩ መድረሳ ሸኾች፣ ትልልቅ ዓሊሞች በህሉል ዘንድ እየሄዱ ይታረሙ፣ ተማሪዎቻቸውን ይዘው እየሄዱ ትልቅ ትምህርት ያስቀስሙ ነበር።

**በህሉልና ሸይኽ ጁነይድ**

ሸይኽ ጁነይድ አል-በግዳዲ ከተማሪዎቻቸው ጋር ጥቂት ለመጓዝ ከከተማዋ ወጣ ብለው ነበር። መንገድ ላይ ሳሉ ሸይኹ ስለ በህሉል ጠየቁ፤ ተማሪዎቹ ‹‹እብድ ነው እኮ፤ ከሱ ምን ፈልገው ነው?›› አሏቸው። እንዲመጣ ንገሩልኝ፤ ከርሱ ምፈልገው

Edit with WPS Office

አንድ ነገር አለ›› አሏቸው፡፡ ተማሪዎቹ አወየተዟዟሩ በህሉልን በየቦታው ሲያስሱ ቆይተው እበረሃው ሜዳ ላይ አገኙት፤ ሸይኽ ጁነይድንም ወደሱ አመጧቸው፡፡

ሸይኽ ጁነይድ በህሉልን ቀርበው ሲያዩት ከአናቱ ላይ ጡብ አስቀምጦ በተጨነቀ ሁኔታ ላይ ሆኖ አገኙት፡፡ ሸይኹ ሰላምታ አቀረቡ፡፡ በህሉል አጸፋውን መለሰና

‹‹አንተ ማን ነህ?›› ብሎ ጠየቃቸው

‹‹የበግዳዱ ጁነይድ ነኝ›› አሉ

‹‹አቡል ቃሲም ማለት ነህ?›› ድጋሚ ጠየቃቸው

‹‹አዎ እኔ ነኝ›› ብለው አረጋገጡለት

‹‹እንዴት መብላት እንዳለብህ ታውቃለህ?›› በህሉል ጥያቄውን ጀመረ

‹‹አዎ አውቃለሁ፤ በአላህ ስም ጀምሬ ፊት ለፊቴ ከሚገኘው እመገባለሁ፡፡ የምጎርሰው ትንሽ ትንሽ ሲሆን ከአፌ በቀኝ በኩል አድርጌ በዝግታ አላምጣለሁ፡፡ ሌሎች የሚጎርሱትን መጠን አላይም፤ በጎረስኩኝ ቁጥር አላህን አስታውሳለሁ፡፡ የምበላው ምንም ያህል ትንሽ ቢሆን፡ ለእያንዳንዱ ማእድ ጌታዬን አመሰግነዋለሁ፤ ከመመገቤ በፊትና በኋላም እጆቼን እታጠባለሁ፡፡ ብለው መለሱ፡፡

በህሉል የሸይኽ ጁነይድን መልስ ሲሰማ ብድግ ብሎ ቆመ ‹‹ለዓለም የሚተርፍ መንፈሳዊ መምህር መሆን ትፈልጋለህ፤ ነገር ግን ምግብ እንዴት መብላት እንዳለብህ እነኳን አታውቅም›› ብሎ ጥሏቸው ሄደ፡፡ ተማሪዎቹ ‹‹ሸይኻችን፡ ሰውየው እብድ ነው ብለንዎት ነበር›› አሉ፡፡ ሸይኹም ‹‹አዎ፡፡ ስራዎቹ እጅግ ጥበባማ የሆኑ ‹እብድ› ነው፤ ከአፉ የሚወጡትን ረቂቅ ንግግሮች አድምጡ›› ብለዋቸው በህሉልን እፈልገዋለሁ እያሉ ሊከተሉት ወደ በረሃው ዘለቁ፡፡

Edit with WPS Office

በህሉል እበረሃው መሃል ማረፊያ ቤት አግኝቶ አረፍ ብሏል፤ ሸይኽ ጁነይድ ወደሱ ተጠጉ ‹‹አንተ ማን ነህ?›› አላቸው ‹‹እንዴት መመገብ እንዳለበት የማያውቀው ጁነይድ ነኝ›› አሉ። ‹‹እንዴት መመገብ እንዳለብህ አታውቅም፤ እሺ ይሁን እንዴት መናገር እንዳለብህስ ታውቃለህ?›› ሲል ሌላኛውን ጥያቄ አስከተለ።

‹‹አዎ›› አሉ። ‹‹እንዴት ነው የምትናገረው?››

‹‹የምናገረው በእርጋታ ነው፤ ቀጥታ ወደ ነጥቤ እገባለሁ። ያለ ምክንያት አልናገርም፤ ንግግሬንም አላረዝምም። አድማጮቼ በሚረዱት ልክ መልእክቴን አደርሳለሁ፤ የዚህች ዓለም ሰዎች ወደ አላህና መልእክተኛው እንዲመለሱ እጣራለሁ። ወሬ እያስረዘምኩ ሰዎች እንዲሰለቻቸው አላደርግም...›› እንዲህ እንዲህ እያሉ በሐዲስ የተዘገቡትን የንግግር ስነ-ስርዓቶች ጠቀሱለት።

‹‹አመጋገቡን እንተወው፡ አነጋገርም አትችልበትም›› ብሎ በህሉል ጥሏቸው ሄደ። ተማሪዎቹ አሁንም ‹‹ሸይኻችን፡ አዩት አይደል ይህ ሰው ጤነኛ አይደለም። ከእብድ ምንድነው ምትፈልጉት?›› ብለው በህሉልን እንዲተዉት ወተወቷቸው። ‹‹እኔ እናንተ የማታውቁትን አውቃለሁ፤ እፈልገዋለሁ›› አሉና ከበህሉል ኋላ ኋላ እየሄዱ ደረሱበት። ‹‹ከኔ ምንድነው የምትፈልገው?›› በህሉል ጠየቀ ‹‹እንዴት መብላትና መናገር እንዳለብህ የማታውቀው ሰው፤ እንዴት መተኛት እንዳለብህስ ታውቃለህ?›› ደግሞ ሌላ ጥያቄ! ‹‹አዎ ይህንንማ አውቃለሁ›› አሉ፤ በህሉልም ‹‹መልካም እንዴት እንደምትተኛ ንገረኝ›› አላቸው።

‹‹የዒሻ ሰላት እና የቀኑን መጨረሻ ዒባዳዎች ካጠናቀቅኩ በኋላ የመኝታ ልብስ እቀይራለሁ ከዛ...›› በሐዲስ የተነገሩ የመኝታ አደቦችን ነገሩት። በህሉል ‹‹አሁን እንዴት መተኛት እንዳለብህም ጭምር እንደማታውቅ ተረድቻለሁ›› ብሎ ትቷቸው

Edit with WPS Office

ሊነሳ ሲል ሸይኽ ጁነይድ ልብሱን ጥብቅ አድርገው ያዙና ‹‹በህሉል ሆይ፡ እኔ አላውቅም፤ ስለዚህ እባክህን ለአላህ ብለህ አስተምረኝ›› አሉት። ‹‹መጀመርያውኑ እውቀት ፍለጋ መጥተህ ‹አውቃለሁ› ስትል ነበር እየሸሸሁህ የነበረው፤ አሁን ግን አላዋቂነትህን ስለመሰከርክ አስተምርሃለሁ። በመልሶችህ የዘረዘርካቸው ነገሮች በሙሉ ተቀዳሚ ስርዓቶች እንዳልሆኑ ማወቅ አለብህ። ምግብ ከመመገብ ጀርባ ያለው እውነት ሐላል መመገብህ ነው፤ አንተ በዘረዘርካቸው ስነ- ስርዓቶች ወይም ከመቶ ኣዳቦች ጋር ሐላል ያልሆነልህን ብትመገብም ስርዓት መጠበቅህ አንዳች ፋኢዳ አያስገኝልህም፤ እንዲያውም ልብህን በማጥቆር ሰበብ ዋነኛ ምክንያት ይሆንብሃል›› ብሎ በህሉል ማስረዳት ጀመረ። ‹‹አላህ ታላቅ ምንዳ ይክፈልህ›› አሉ ሸይኽ ጁነይድ፤ በህሉል ቀጥሏል ‹‹ልብ ሁሌም ንጹህ ሆኖ መቆየት አለበት፤ ስለዚህ ምንም ከመናገርህ በፊት ጥሩ እሳቤ (ኒያ) ይኑርህ። ንግግርህም አላህን የሚያስደስት ይሁን! ንግግርህ ለዝች ጠፊ ዓለም ወይም ለማይረባ ስራ ከሆነ ምን ያህል አሰማምረህ ብትናገረው አደጋ ያመጣብሃል እንጂ አይጠቅምህም! ለዚህም ነው ዝምታ እና ፀጥታ ይበልጥ ተወዳጅ የሆኑት››

‹‹ስለ እንቅልፍ ስርዓት የተናገርካቸውም ሁለተኛ ስርዓቶች ናቸው፤ የመጀመርያው እውነት ልብህን ከማንኛውም ቂም፣ ቅናትና ጥላቻ ፅዱ አድርገህ መተኛት ነው›› በማለት የነገሮችን ምክንያት አብራራላቸው። ጁነይድ የበህሉልን እጅ ስመው ዱዓ አደረጉለት፤ ይህን የተመለከቱ በህሉልን አቅለ-ቢስ አድርገው ሲያስቡ የነበሩ ተማሪዎች ሸይኻቸው ትልቅ ትምህርት አስተምረዋቸው አዲስ ህይወት መምራት ጀመሩ። እዚህ ታሪክ ላይ ታላቁ ሸይኽ ጁነይድ ለተማሪዎቻቸው ማስገንዘብ የፈለጉት መልእክት ስላለ እንጂ እርሳቸው ያልተደረዱት ሆኖ እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

Edit with WPS Office

**ከአብደላህ ኢብኑ ሙባረክ ጋር**

አንድ እለት አብደላህ ኢብኑ ሙባረክ ጥበበኛውን በህሉል ለማግኘት ወደ በረሃ ወረደ፡ ከዛ ጭው ካለ ንዳዳማ በረሃ መሃል በህሉል በባዶ እግሩ አናቱ ላይ ሌጣ ጨርቅ እንኳን ጣል ሳያደርግ መሬት ላይ ተቀምጦ አላህን እያወሳ አገኘው። ተጠግቶ ሰላምታ አቀረበለት፡ በህሉልም አፀፋውን መለሰ። አብደላህ ‹‹ያ ሸይኽ፡ ምከረኝ። ይችን ዓለም እንዴት ከወንጀል ርቄ መኖር እንዳለብኝ እንድታሳየኝ ነው የመጣሁት። ሀጢአቶቼ በረከቱ፡ የነፍስያዬን ፍላጎቶች መቆጣጠር ተስኖኛልና እባክህ እረፍት የማገኝበትን መንገድ ብትጠቁመኝ ብዬ ነው አመጣጤ›› ሲል በተማፅኖ መልክ ጠየቀው። በህሉልም ‹‹አብደላህ ሆይ፡ እኔ ለራሴ ጭንቀት ያናጠበኝ፣ ለነፍሴ መላ ያጣሁ ሆኜ ሳለ ከኔ ምን ፈልገህ ትመጣለህ? ማሰብ የምችል ብሆን ኖሮ ሰዎች ‹እብድ› ብለው ይጠሩኝ ነበር? የእብድ ምክር ማን ይሰማና ይቀበላል! ስለዚህ ሂድ....ብልህና አስተዋይ ሰዎችን ፈልግ›› አለው።

‹‹አንተ ሸይኽ ራሳቸውን እብድ ብለው የሚጠሩ ሌሎችን እያሞኙ እንደሆነ አውቃለሁ፡ እንዲያውም ከሁሉም ይበልጥ ብልህ እነሱ ናቸው። እውነተኛ ቃል ከእብዶች ብቻ ነው የሚወጣው›› አለ አብደላህ። በህሉል ዝም አለ፡ ከበረሃው ላይ በሁለቱ ሰዎች መካከል ዝምታው ረዘመ። አብደላህም ‹‹እባክህ አታስከፋኝ፡ ያንተን ምክር ፍለጋ ነው እዚህ ድረስ የመጣሁት›› እያለ በህሉል እንዲናገር ይወተውት ጀመር

‹‹አብደላህ ሆይ፡ የእብድ ምክር ሰምተህ ቃልህን እንዳታጥፍ፡ በመጀመርያ አራት መስፈርቶች አሉኝ። በነሱ ከተስማማህ በኋላ ምክሬን እለግስሃለው፡ ባርነትህን

Edit with WPS Office

የሚያፀናልህን ሚስጥርም አካፍልሃለው›› አለው።

አብደላህ፡ ‹‹አራቱ መስፈርቶች ምንድን ናቸው? ልወቃቸውና እስማማለሁ››

በህሉል፡ ‹‹የመጀመርያው መስፈርት ኀጢአት በምትሰራበት ጊዜ ወይም ከአላህ ፍላጎት ውጪ በምትሆንበት ወቅት የሱን ሲሳይ አትጠቀም››

አብደላህ፡ ‹‹ከሱ ውጪ የሚረዝቅ የለ! ታድያ የማንን ሲሳይ እጠቀማለሁ?››

በህሉል፡ ‹‹ብልህ ዓሊም ነኝ ብለህ ትሞግታለህ፡ አላህን አመልካለሁ እሱ የሚለግሰኝን እመገባለሁ ትላለህ፡ በዚህ በኩል ደግሞ ከትእዛዙ ታፈነግጣለህ እስቲ ራስህ ፍረድ ይህ ነው ለችሮታው ምላሽ የሚሆነው?››

አብደላህ፡ ‹‹የተናገርከው ሁሉ ሐቅ ነው፡ ሁለተኛው መስፈርት ምንድን ነው››

በህሉል፡ ‹‹ኀጢአት መስራት በምታስብ ጊዜ ከርሱ ግዛት ክልል ውጪ ሁን››

አብደላህ፡ ‹‹ከመጀመርያው ይልቅ ከባድ ነው፡ ሁሉም ቦታ የአላህ ንብረትና ግዛት ሆኖ ሳለ ወዴት መሸሽ እችላለሁ?››

በህሉል፡ ‹‹እሱ የለገሰህን እየተመገብክ፡ በሱ ግዛት ውስጥ እየኖርክ ከእሱ ፍላጎት ማመፅ ምን የከፋ ስራ ነው! አሁንም አንተው ፍረድ ችሮታ እንዲህ ነው የሚመሰገነው?››

አብደላህ፡ ‹‹ተቀብያለሁ፡ እሺ ሶስተኛው መስፈርትስ ምንድን ነው?››

በህሉል፡ ‹‹በሶስተኛ ደረጃ፡ አንድ ወንጀል ለመስራት ስታስብ እሱ ወደማያይህ ቦታ ሄደህ ተደበቅ፡ ከዚያ የፈለግከውን መስራት ትችላለህ››

አብደላህ፡ ‹‹ይህ ደግሞ በጭራሽ የማይሆን ነው! አላህ እኮ ሁሉንም ነገር ያያል፡ ያውቃልም። ሁሉም ቦታ ያለ አምላክ ነው፡ ፍጥረታቶቹ በሙሉ የሚሰሩትን ይከታተላል››

Edit with WPS Office

በህሉል፡ ‹‹እውነትም አንተ ብልህ ሰው ነህ፡ አላህ ሁሉም ቦታ እንደሚገኝ ታውቃለህ። ሁሉን አዋቂ እና ሁሉን ተመልካች ጌታ እንደሆነ ታምናለህ። በዚህ ሁኔታ የሱን ሲሳይ እየተጠቀምክ፣ በሱ ግዛትና መሬት እየኖርክ፣ እሱም ሁሉን አዋቂ እና ተመልካች ሆኖ እያለ እርሱን ማመፅህ ምን ይባላል!...››

አብደላህ፡ ‹‹የተናገርከው ሁሉ እውነት ነው፡ አራተኛውን ቅድመሁኔታ ንገረኝ››

በህሉል፡ ‹‹አራተኛው ደግሞ የሞት መልአክ አዝራኤል የአላህን ትእዛዝ ሊፈፅም፣ ነፍስህን ለማውጣት በሚመጣብህ ጊዜ ‹ቆይ ትንሽ ጊዜ ጠብቀኝ፡ ወዳጆቼን ልሰናበት፡ ለመጨረሻው ጉዞዬ ትንሽ ስንቅ ልጨምር፡ በኋላ ነፍሴን ትወስዳታለህ› በለው››

አብደላህ፡ ‹‹እማይሆነውን! ይህ ደግሞ ከሁሉም መስፈርቶች ከባድ ነው፡ የዚያኔኮ መለከል መውት የአንድ ትንፋሽ ጊዜ ያህል እንኳ አያቆየኝም››

በህሉል፡ ‹‹አንተ ታላቅ ሰው፡ ከሞት የሚያድንህ እንደሌለ ታውቃለህ፡ ልትሸሸው አትችልም። ጊዜህ አብቅቶ መልአኩ ሲመጣብህ ተጨማሪ ደቂቃ አይፈቀድልህም። ወንጀል ላይ እያለህ፣ ኀጢአት እየሰራህ በድንገት ይመጣብህ ይሆናል። እስትንፋስ መጨመር እንኳ አይቻልህም፡ አላህ እንዳለው ነው የሚሆነው ‹‹ለሕዝቦም ሁሉ የተወሰነ ጊዜ አላቸው። ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት አንዲትን ሰዓት አይቆዩም። (ከጊዜያቱ) አይቀደሙምም››

እና ወዳጄ አብደላህ ሆይ፡ የእብድ ምክር የምትሰማ ከሆን እኔ የምነግርህ ይህንን ነው። ከዝንጋቴ እንቅልፍ ንቃ! እብሪተኛነትን እና ፈንጠዝያን ተጠንቀቅ አደራ። ጭንቀትህ ለቀጣዩ ዓለም ብቻ ይሁን! ይህች ቅርቢቱ ዓለም አጭር ሆና ኋላ የሚጠብቅህ ግን ረዥም ጉዞ ነው። የዛሬን ስራ ለነገ አታሳድር፡ ምናልባት አንተ

Edit with WPS Office

ነገን ላትደርስበት ትችላለህ። የተሰጠህ ‹አሁን› ብቻ መሆኑን እወቅ። ለቀጣዩ ዓለም በምትሰራቸው ስራዎች አትሳነፍ፡ ለነገው ዓለም ዛሬ ቀድመህ ተዘጋጅ። ወደዛ ከተሻገርክ በኋላ ፀፀት ምንም ፋይዳ የለውም››

አብደላህ ኢብኑ ሙባረክ ይህን ሲሰማ ከጭንቅላቱ አቀርቅሮ በሀሳብ ዓለም ሰመጠ። ለረዥም ጊዜ ዝም አለ፡ በህሉልም ‹‹አብደላህ ሆይ፡ ለነገህ የሚጠቅምህን ምክር ፈልገህ፣ ምሳሌ የሚሆንህን ሽተህ መጥተሃል። ለምን አንገትህን ትደፋለህ? በፍርዱ ቀን ጠንካራና አስፈሪ መላእክት ሲጠይቁህ ምን ምላሽ ይኖርሃል? ነገር ግን ዛሬ የነፍሱን ሂሳብ የሰራ ሰው ነገ ፍርሃት አያገኘውም››

አብደላህ ቀና አለና ‹‹አንተ ሸይኽ፡ በሙሉ ልቤ ምክርህን አዳምጫለሁ። አራቱንም መስፈርቶች ተቀብያለሁ። አንድ ነገር ጨምርልኝና ተማሪህ ተከታይህ አድርገኝ›› አለ። በህሉልም ‹‹አብደላህ ሆይ፡ ባርያ ምንም አይነት ስራ ቢሰራ በአላህ ትእዛዝ ነው የሚያደርገው፡ የሚናገረውም ሆነ የሚያዳምጠው በርሱ በጌታው ፍላጎት ነው። ባርያ ሁሌም ባርያ ነው›› ብሎ በመጨረሻ ምክሩን ቋጨ።

*************

ስለሱ የከተቡ ሰዎች 'The wise fool of Baghdad' ይሉታል፡ ከሰዎች ግርግርና ሁካታ ራሱን አግልሎ ማህበረሰቡ ላይ ያሉ ችግሮችን መሪዎች ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ያለ አንዳች ፍርሃት ይናገራል። ተወቃሾችን ይወቅሳል። ከንጉሱ ሃሩን ጀምሮ ከበህሉል ተግሳፅ ያመለጠ ባለስልጣን የለም። በተለይ ሃሩን አል-ረሺድ ከንግግሮቹ ጥበብ ይቀስም ስለነበር ብዙ ጊዜ ይወዳጀዋል። ባለቤቱ ዙበይዳን

Edit with WPS Office

ጨምሮ ምክር ያሻቸው ጊዜ በህሉልን ይፈልጉ ነበር።

**የበህሉል ምክር**

ኸሊፋው ሃሩን ምክር ፍለጋ በህሉል ዘንድ ሄደ፤ ‹‹ሃሩን ሆይ፡ እልም ያለ በረሃ ውስጥ ነው ያለኸው እንበል፤ አንዲት ጠብታ ውሃ አጥተህ ከፍተኛ የውሃ ጥም አያሰቃየህ ለሞት ተቃርበሃል። ጥምህን ቆርጦ ወደ ህይወት ለሚመልስህ አንድ ኩባያ ውሃ ምን ያህል ትከፍላለህ?›› በህሉል ጠየቀ

ሃሩን ኒ‹‹የወርቅ ሳንቲሞችን እከፍላለሁ›› ሲል መለሰ

‹‹የውሃው ባለቤት ውሃውን በወርቅ ሳንቲሞች ለመለወጥ ፍቃደኛ ባይሆንስ ምን ትሰጣለህ?››

‹‹ከንግስናዬ ግማሹን አካፍለዋለሁ›› አለ። በህሉል ቀጠለና

‹‹መልካም፡ ያን ውሃ ጠጥተህ መሽናት የማያስችል በሽታ ታመምክ፤ ይህን በሽታህን ለሚያድንልህ ሰው ምን ትከፍለዋለህ?››

‹‹የተቀረውን ግማሽ ግዛቴን አስረክባለሁ›› አለ።

‹‹ስለዚህ ሃሩን ሆይ፡ በንግስናህ አትመካ! ይጠቅመኛል ብለህም እንዳታስብ፡ ከአንድ ብርጭቆ ውሃ የበለጠ ዋጋ የለውምና። ጭንቀትህን ለንግስናህ ከምታደርግ ይልቅ ለአላህ ፍጡራን በጎ ብትውል አይሻልም?›› ብሎ በህሉል ድንቅ ምክሩን በአስገራሚ መንገድ አካፈለው

Edit with WPS Office

**የሃሩን ጥያቄና የበህሉል መልስ**

ሃሩን አል-ረሺድ ከሐጅ ጉዞው በመመለስ ላይ እያለ በህሉል ከመንገዱ አለፍ ብሎ እየጠበቀው ነበር። የሃሩንን መምጣት ሲመለከት ሶስት ጊዜ ‹‹ሃሩን፡ ሃሩን፡ ሃሩን›› እያለ ጮሆ ተጣራ። ‹‹ማነው እንደዚህ የሚጠራኝ?›› ብሎ ሲጠይቅ አብረውት የነበሩ ሰዎች በህሉል መሆኑን ነገሩት። ‹‹ወደኔ አምጡልኝ›› ብሎ አዘዘ፤ በህሉል አጠገቡ እንደደረሰ ሃሩን በህሉልን ‹‹እኔ ማን ነኝ?›› ብሎ ጠየቀው

‹‹አንተ ማለት ያ፡ ሰዎች ደካሞችን በሚበድሉ ጊዜ ተጠያቂ የሆንክ ሰው ነህ›› አለው። ሃሩን ማልቀስ ጀመረ፤ ‹‹እውነት ነው የተናገርከው፡ አሁን ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ›› ሲል ጥያቄውን አስከተለ

‹‹የኔ ጥያቄ ሃጢአቶቼን በሙሉ ምረህልኝ ጀነት እንድታስገባኝ ነው›› በህሉል ፍላጎቱን ተናገረ። ‹‹ይህ እኮ እኔ የምችለው ነገር አይደለም! ባይሆን እዳዎችህን ልክፈልልህ›› አለው

‹‹እዳን ባለእዳ አይከፍልም፤ አንተ ራስህ የህዝቡ እዳ አለብህ። ስለዚህ ለህዝቡ ሀብቱን መልስለት፤ የሌላ ሰው ንብረት ለኔ መስጠት መልካም ስራ አይሆንህም›› አለው። ኸሊፋውም ‹‹እሺ ከግምጃ ቤት ጥቂት ገንዘብ እንዲደርስህ ላድርግ፤ ካሁን በኋላ ቀለል ያለና ምቹ ህይወት እንድትኖር እፈልጋለሁ›› አለው። በህሉል ‹‹ሁላችንም የአላህ ባሮች ነን፤ ምንዳ የምንከጅለው ከርሱ ብቻ ነው። አንተን እያኖረ እኔን የሚረሳኝ ይመስልሃል? አሁን ይህን ገንዘብ ከሰበሰብክባቸው ሰዎች እንዲመለስ አድርግ። ዛሬ ካላደረግከው ኸሊፋው ያለበትን እዳ እንዲከፍል የሚደረግበት ቀን ይመጣል፤ ያ ቀን ግን ኸሊፋው እጁ ላይ አንዳች ነገር

Edit with WPS Office

አይኖረውም፤ ከጸጸትና ሀፍረት በስተቀር ምንም አያገኝም›› አለው፡፡ ሃሩን በበህሉል ንግግር ልቡ ተነክቶ ተንሰቅስቆ ማልቀስ ጀመረ፤ ምክሩንም በተግባር ላይ አዋለው፡፡

ሃሩን አል-ረሺድ ከባለሟሎቹ ጋር ነበር፡ እብዱ በህሉል አብሯቸው እየተጓዙ ነው፡፡ ጫካው ውስጥ እንደገቡ አንድ አጋዘን አይናቸው ገባች፡ ሃሩን ቀስቱን አስወንጭፎ ወረወረ፡፡ አጋዘኗን ግን አላገኛትም፡ ሳታት

‹‹ጎበዝ!›› አለ በህሉል

‹‹እየተሳለቅክብኝ ነው?›› ሃሩን በንዴት ጠየቀው

‹‹አይደለም፡ አጋዘኑ ስላመለጠና ራሱን ስላዳነ ተደስቼ ነው›› አለው

በርግጥ ሱፊዮች እዝነታቸው ለእንስሳትም የተረፈ ነበር፡፡ ጉንዳንን እንኳን አይጎዱም፡፡ በሚራመዱ ጊዜ ነፍሳትን እንዳይጨፈልቁ ተጠንቅቀው ነው፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ እግራቸው ላይ ቃጭል እስከማሰር የደረሱም አሉ፡ እንስሳት ድምጹን ሰምተው እንዲሸሹ ለማድረግ፡፡

*************

በህሉል ምክሮቹ መንፈሳዊነት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡ ግብረ-ገብ እና ፍልስፍና ነክ ጉዳዮቹም በርካታ ናቸው፡፡ ሰዎች በብዛት የሚሰባሰቡበት የበግዳድ ገበያ ቦታ መጫወቻ ሜዳው ነበር፡ ማጭበርበሮች እና ማታለሎች የሚበረክቱበት ስፍራ በመሆኑ ተጠቂ ሰዎችን ይረዳበታል፡ ግፍንም ይቃወማል፡፡

Edit with WPS Office

**የበህሉል ፍርድ**

ረሃብ የጠናበት ዐረብ በግዳድ ከተማ ውስጥ ይለምናል፡ አንድ ምሽት በምግብ ቤት በኩል እያለፈ ሳለ የተለያዩ ምግቦች ቃና አወደው፡፡ ሆዱ ተገላበጠ፡ የሚመዘምዘውን አንጀቱን ለማሳረፍ ሲል ቆሞ ሽታውን መማግ ጀመረ፡፡ ምንም ሳንቲም ስላልነበረው ከፍሎ መመገብ አልቻለም፡፡ ያደረ ደረቅ ዳቦ ከአቁፋዳው ውስጥ አወጣና ከሚንተከተከው ምግብ የሚወጣውን እንፋሎት እያሞቀ እያለሰለሰ መብላት ጀመረ፡፡ የምግብ ቤቱ ባለቤት ዝም ብሎ እተመለከተው ነው፡ ለማኙ ዳቦውን በልቶ ሲጨርስ ለመሄድ ተነሳ፡፡ ነገር ግን የቤቱ ባለቤት አስቆመው፤ አስቆመውና ሂሳብ ክፈል አለው

‹‹እንዴት ነው ምከፍለው ያንተን ምግብ አልበላሁ!››

‹‹ትከፍላለህ ከኔ ምግብ ተጠቅመሃል››

ከፍተኛ ጭቅጭቅ ተፈጠረ፡ በአጋጣሚ በህሉል በዚያ በኩል እያለፈ ስለነበር የነገሩን ምንነት ለማጣራት ወደ ውስጥ ገባ፡፡ ዐረቡ ሰውዬ በህሉል እንዲዳኛቸው ጠየቀ

‹‹ይህ ሰው ምግብህን በልቷል ወይስ አልበላም?›› በህሉል ባለምግብ ቤቱን ጠየቀው፡፡ ‹‹በርግጥ ምግቤን አልበላም፡ ግን ከእንፋሎቱ ተጠቅሟል›› አለ

‹‹እንደዛ ከሆነ ተክክል ነህ›› አለ በህሉል ‹‹ይኸውልህ›› አለና ከኪሱ ሳንቲሞች አወጣ፡ አንድ በእንድ እያወጣ በየተራ ሁሉንም አሳየው፡ ከዚያ መሬት ላይ ዘረገፋቸው፡ እንደገናም ለቀማቸውና ‹‹የሳንቲሞቹን ድምፅ ውሰድ›› አለው

‹‹ምን ይሉት አከፋፈል ነው ይሄ ደግሞ!?›› ባለ ምግብ ቤቱ ተገርሞ ጠየቀ

Edit with WPS Office

‹‹የኔ ፍትሃዊ ፍርድ እንደዚህ ነው፡ ሽታ እና እንፋሎት የሚሸጥ ሰው ሊከፈለው የሚገባው የሳንቲም ድምፅ እና ቅጭልታ ነው›› ብሎ በህሉል ድንቅ ምላሽ አስቀመጠ

***************

እብድ መስሎ እውነትን የኖረ፡ ሰዎችን ከስህተት መንገድ ለመመለስ፣ ለተራው ህዝብ ፍትህ ለማስጠበቅ፣ ጤነኝነቱን አሳልፎ የሰጠ ነው። በአልነይሳቡሪ "ዑቀላእ አልመጃኒን" ስራ በእስልምና ታሪክ በርካታ እንደ እብድ እየተቆጠሩ የኖሩ ሰዎች ተዘክረዋል። ማንም ደፍሮ የማይናገረው 'ሐቅ' የሚያራምዱ፣ በሰዎች ተንቀው ነገር ግን ህዝብን ያቀኑ ሰዎች ስም ዝርዝር አስቀምጧል። በህሉል ከሁሉም በይበልጥ ታዋቂ ታሪኩም ተሻጋሪ ሆኖ ቆይቷል። በ2007 እ.ኤ.አ የሶሪያ ሚዲያ ታሪኩን በሶስት ምእራፍ ተከታታይ ፊልም ሰርተው ለህዝብ ተደራሽ አድርገዋል።

**በህሉል እና ነጋዴው**

አንድ ቀን ከበግዳድ የመጣ ነጋዴ በህሉልን አገኘውና ‹‹ሸይኽ በህሉል፡ እባክህ ብዙ ትርፍ የሚያስገኝልኝን፣ ገዝቼ የምነግድበት እቃ ጠቁመኝ›› ሲል ምክር ጠየቀው። በህሉልም ‹‹ብረትና ጥጥ ነግድ›› ብሎ ጥቆማውን ሰጠ። ሰውየው ወደ ገበያ ሄዶ ብረትና ጥጥ በብዛት ገዝቶ አከማቸ። ያጠራቀመውን ቀስ በቀስ እየሸጠ ከወራት በኋላ እጅግ ትረፋማ ሆነ።

ከጊዜያት በኋላ በድጋሚ በህሉልን አግኝቶ ጠየቀው፤ ‹‹አንተ እብድ በህሉል፡ አሁንስ ምን ገዝቼ ብሸጥ ያዋጣኛል?›› አለው። በህሉል ‹‹በአሁኑ ደግሞ ሽንኩርት እና ሀብሀብ ግዛ›› ብሎ መከረው። ሰውየው ወደ ገበያ ሄዶ በሙሉ ገንዘቡ

Edit with WPS Office

ሽንኩርት እና ሀብሀብ ገዝቶ ተመለሰ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን የገዛቸው እቃዎች መበላሸትና መበስበስ ጀመሩ። ገንዘቡም በጠቅላላ ከሰረ። ሰውየው በንዴት ጦፎ በህሉልን ፍለጋ አመራ። ልክ አንዳገኘው

‹‹መጀመርያ ምክር የጠየቅኩህ ጊዜ ብረትና ጥጥ ብለኸኝ ብዙ አተረፍኩ። ለሁለተኛ ጊዜ ስጠይቅህ ግን ምን አይነት ጥቆማ ነው የሰጠኸኝ ሀብቴ በጠቅላላ ጠፋ ከሰርኩ›› እያለ መጮህ ጀመረ። በህሉልም እንዲህ ሲል የነገሩን ሚስጥር መለሰለት

‹‹በመጀመርያ ቀን ስታናግረኝ ሸይኽ በህሉል ብለህ ጠራኸኝ፣ እንደ ብልህ ሰው ስላናገርከኝ የጥበበኛ ሰው ምላሽ ሰጠሁ። በሌላኛው ቀን ደግሞ ‹አንተ እብድ በህሉል› አልከኝ እኔም የእብድ ምክር መከርኩህ›› አለው። ነጋዴው ባሳየው ባህሪ ሀፍረት ተሰምቶት ከበህሉል ጥሩ ትምህርት ቀስሞ ሄደ።

Edit with WPS Office